# ዜና አመዝኤ



## በዚህ እትም ውስጥ


ለኢትዮጵያ የሚደደረገው ሰብዓዊ ዕርዳታ ተጠናክሮ የሚቀጥልበትን ሁኔታ እንደሚያመቻች የሳውዲ ዐረቢያ ልዑካን ቡድን ገለፀ

ገጽ 2

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ለውይይት ቀረበ

ገጽ 3

የበልግ ሰብል አዝመራና የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ሁኔታ ለመገምገም አጥኚ ቡድኖች ተሠማርተዋል

ገጽ 5

ባለፉት ሦስት ወራት ከ1.1 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተጓጓዟል

ገጽ 5

ከድርቅ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ የጤና ችግሮችን ለመከላከል የተደረገው የተቀናጀ ጥረት ውጤታማ እንደነበር ተገለፀ

ገጽ 7



በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ
ስልክ. 529259
529262
ጠ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ፣ www.dppc.gov.et




# በኢትዮጵያ ያለው የምግብ ዋስትና ችግር በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊቀረፍ እንደሚችል ተገለጸ

መንግሥት በቀየሳቸው ስትራቴጂዎች አማካይነት እየተተገበሩ ባሉ የልማት ሥራዎች ዓለም አቀፍ ለጋሽ መንግሥታትና ድርጅቶች ከመንግሥት ጎን በመቆም እያደረጉ ባሉት ያላሰለሰ ድጋፍ የተመዘገቡት አበረታች የዕድገት ውጤቶች በኢትዮጵያ የሚታየው የምግብ ዋስትና ችግር በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊቀረፍ እንደሚችል ያመላከተ መሆኑን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ሲሞን መቻለ ገለፁ።



ዋና ዳይሬክተር ሲሞን መቻለ ይኸንን የገለፁት አመዝኤ በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ዙሪያና መንግሥት ችግሩን ለዘለቄታው ለመፍታት በነደፈው የምግብ ዋስትና ኘሮግራም አማካይነት እየወሰደ ስላለው እርምጃ የአውስትራሊያ ምክር ቤት አባል ለሆኑት ለሴናተር ስቲቭ ፊልዲንግ ሰኔ 28 ቀን 1998 ዓ.ም በኤጀንሲው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ገለፃ ባደረጉበት ወቅት ነው።

ዋና ዳይሬክተሩ በዚሁ ጊዜ እንደተናገሩት ኢትዮጵያ ከለጋሽ ሀገራት ሰብዓዊ ዕርዳታ ከሚቀርብላቸው ሀገራት በዋነኛነት ብትጠቀስም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሀገሪቱን ከድህነት ለማውጣትና በምግብ ራሷን እንድትችል ለማድረግ በሚሰጥ የልማት ድጋፍ ረገድ የምታገኘው ዕርዳታ ዝቅተኛ እንደሆነ አመልክተዋል። በተለያዩ ምክንያቶች ለአደጋ የተጋለጡትን ወገኖች ሕይወት ለመታደግ የሰብዓዊ ዕርዳታ አስፈላጊነት የማይታለፍ ቢሆንም ህዝቡ ጥሪት እንዲያካብት እና ከድህነት ወጥቶ ራሱን መመገብ በሚያስችለው የተለያዩ የልማት እርዳታዎች መደገፍ ደግሞ ችግሩን እስከወዲያኛው ለማስወገድ መንግሥት እያካሄደ ላለው ጥረት የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን አቶ ሲሞን ተናግረዋል።

በማያያዝም በዚህ ረገድ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በዋነኛነት በተያዘው የምርታማ ሴፍትኔት መርሀ ግብር ለሚሳተፉ አርሶ አደሮች የሚያስፈልገውን የምግብና የገንዘብ እርዳታ በማቅረብ የአንዳንድ ለጋሽ ሀገራትና ድርጅቶች ድጋፍ የሚያበረታታ እንደሆነ ገልፀዋል። በዚህ ረገድ የሚደረገው ድጋፍ ሰፊና ገና በጅማሮ ላይ በመሆኑ

ለቀጣይነቱ የሁሉንም ርብርብ የሚጠይቅ እንደሆነም አሳስበዋል፡፡

የአውስትራሊያው ም/ቤት አባል ሴናተር ስቲቭ ፊልዲንግ በበኩላቸው የተደረገላቸው ገለፃ በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው የሰብአዊ ዕርዳታ ሁኔታና ለወደፊቱም ሀገሪቱ ከድህነት በመላቀቅ ራሷን ለመቻል በምታደርገው ጥረት ስለሚፈለገው ድጋፍ በሚገባ ለመገንዘብ እንዳስቻላቸው ገልፀዋል፡፡ አያይዘውም ይህንኑ እውነታ ወደሀገራቸው ሲመለሱ አውስትራሊያ ለኢትዮጵያ በምታደርገው ሰብአዊ ድጋፍ ዓይነትና ሁኔታ ላይ ከሀገራቸው መንግሥት አመራር አካላት ጋር በመመካከር በድህነት ውስጥ ያለውን በተለይም በገጠር የሚኖረውን ህዝብ ይበልጥ ተጠቃሚ የሚያደርግ ድጋፍ እንዲገኝ የበኩላቸውን ጥረት እንደሚያደርጉ ተናግረዋል፡፡

## ለኢትዮጵያ የሚደደረገው ሰብዓዊ ዕርዳታ ተጠናክሮ የሚቀጥልበትን ሁኔታ እንደሚያመቻች የሳውዲ ዐረቢያ ልዑካን ቡድን ገለፀ

ሳውዲ አረቢያ ለኢትዮጵያ የምታደርገው ሰብዓዊ ዕርዳታ የሚያድግበትንና ተጠናክሮ የሚቀጥልበትን ሁኔታ እንደሚያመቻች በሰብዓዊ ዕርዳታ እና ተዛማጅ ጉዳዮች ዙሪያ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመጎብኘት ወደ ኢትዮጵያ የመጣው የሳውዲ አረቢያ መንግሥት ልዑካን ቡድን ገለፀ፡፡

ሳውዲ አረቢያ ለኢትዮጵያ የምታደርገው ሰብዓዊ ዕርዳታ የሚያድግበትንና ተጠናክሮ የሚቀጥልበትን ሁኔታ እንደሚያመቻች በሰብዓዊ ዕርዳታ እና ተዛማጅ ጉዳዮች ዙሪያ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመጎብኘት ወደ ኢትዮጵያ የመጣው የሳውዲ አረቢያ መንግሥት ልዑካን ቡድን ገለፀ፡፡

የልዑካን ቡድኑ መሪ የሆኑት በሳውዲ



አረቢያ የገንዘብ ሚኒስቴር የወጪዎች ዋና መምሪያ ዋና ዳይሬክተር ሞህመድ አብዱ ራህማን አል-ሙጌቲብ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ሲሞን መቻለ ጋር በኤጀንሲው የስብሰባ አዳራሽ ከሰብዓዊ ዕርዳታዎች ጋር በተያያዘ የሀገሪቱ እየተከናወኑ ባሉ ሥራዎች ዙሪያ በተመካከሩበት ወቅት እንደተናገሩት ሳውዲ አረቢያ እና ኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜያት የቆየ ታሪካዊ ግንኙነት ያላቸው እንደመሆናቸው መጠን ሳውዲ አረቢያ በኢትዮጵያ ለሚፈለገው ሰብዓዊ ዕርዳታ የበኩሏን አስተዋጽዖ ስታበረክት ቆይታለች፡፡

በኢትዮጵያ የሚያደርጉት የዚህ ጉብኝት ዋነኛ ዓላማ በሰብዓዊ ዕርዳታና በልማት ረገድ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን በግንባር ለማየት እና በዚሁ ዙሪያ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣናት ጋር በመመካከር አስፈላጊው ድጋፍ የሚደረግበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እንደሆነ የገለፁት ሚስተር ሞህመድ ቡድናቸው ጉብኝቱን አጠናቆ ሲመለስ የሀገራቸው መንግሥት በኢትዮጵያ ሰብዓዊ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች እስካሁን ሲያደርገው ከነበረው ድጋፍ በተጨማሪ በዘርፉ ለሚደረገው እንቅስቃሴ የአቅም ግንባታ ድጋፍ እና ሥር በሰደደ ድህነት ሳቢያ ለምግብ ዋስትና ችግር የተጋለጠው የገጠሩን ህዝብ ከድህነት ለማላቀቅ በሚያስችሉ የልማት ሥራዎች ረገድ

አስፈላጊውን ዕርዳታ እንዲለግሥ ጥረት እንደሚያደርጉ ገልፀዋል።

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ሲሞን መቻለ በበኩላቸው የሳውዲ አረቢያ መንግሥት ኢትዮጵያ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለምታቀርባቸው የሰብዓዊ ዕርዳታ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠቱን አስታውሰው ፣ ይኸው ድጋፍ የኢትዮጵያ መንግሥት በቁርጠኝነት ድህነትን ለማስወገድና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የጀመረው እንቅስቃሴ ግቡን እስኪመታ ድረስ በተለያየ መልኩ ይቀጥላል የሚል እምነት አለን ብለዋል።

አቶ ሲሞን በማያያዝም በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎችን የማቅረቡ አስፈላጊነት እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት በ5 ዓመታት ውስጥ በሀገሪቱ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ስትራቴጂ ነድፎ እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ መደገፍ ደግሞ ችግሩን ለዘለቄታው ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ ከአጋር ሀገራትና ድርጅቶች የሚፈለግ ዋነኛ ድጋፍ ነው። በመሆኑም በዚህ መስክ የተሰማሩትን ተቋማት አቅም በማጎልበትም ሆነ የገጠሩን አርሶ አደር በምግብ ራሱን እንዲችል ለሚያካሂዳቸው የልማት ሥራዎች አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በሚደረገው የተቀናጀ ጥረት ሁነኛ አስተዋፅዖ ያበረክታል ብለዋል።

በማከልም ዋና ዳይሬክተሩ የሳውዲ አረቢያ መንግሥት በኢትዮጵያ ለሚቀርቡ የሰብዓዊ ዕርዳታ ፍላጎቶች ከዚህ ቀደም ላደረጋቸውም ሆነ ከዚህ በኋላ ለሚያደርጋቸው አስተዋጽዖዎች በራሳቸውና በተረጂው ህዝብ ስም ምስጋና አቅርበዋል።

## የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ለውይይት ቀረበ

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የቀጣዩ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ረቂቅ ሰነድና ያለፉት ሦስት ዓመት ስትራተጂክ ዕቅድ አፈፃፀም ሰኔ 23 ቀን 1998 ዓ.ም ለሥራ አመራር ውይይት ቀረበ።

እንደሚውል የሚጠበቀው ዕቅዱ በ17 ዋና ዋና ርዕሶች የተከፈለ ሲሆን ኤጀንሲው ስለሚኖረው ራዕይ፣ ተልዕኮ አላማና ግቦች፣ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል ሁኔታ፣ ያለፈው ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ፣ የኤጀንሲው የስልጣን ወሰን ትንተና፣



አስፈላጊው ውይይትና የማሻሻያ ሀሳቦች ታክለውበት እንዲሁም ለጊዜው ሳይጠናቀቅ የቀረው በጀትን የተመለከተው ክፍል ተጠናቆ በሚመለከተው አካል ከፀደቀ በኋላ ከ1999 እስከ 2003 ዓ.ም በሥራ ላይ

የኤጀንሲው እሴቶች፣ የባለድርሻዎች ትንተና፣ ወሳኝ ስትራቴጂክ ጉዳዮች፣ የስትራቴጂክ ዕቅዱ ዓላማዎችና ግቦች፣ የቀጣዩ አምስት ዓመት ዝርዝር ዕቅድ ፕሮግራምና ሌሎችም ተካተውበታል።

የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራሞችን ተግባራዊ በማድረግ በኤጀንሲው ውስጥ ቀልጣፋ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓትንና ሥነ ምግባርን ማስፈን ያለፈው በስትራቴጂክ ዕቅድ አላማዎች እንደነበሩና በዚህም አበረታች ውጤት መመዝገቡ በሰነዱ ላይ ተመልክቷል።

ከዕቅዱና እየተተገበረ ከሚገኘው ሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራም ጋር በተያያዘ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያው ያስገኛቸው ለውጦችና መሻሻሎች፣ ለሙስና ቀዳዳ የሚከፍቱ አሠራሮችን በመፈተሽ የተወሰዱ የማሻሻያ እርምጃዎችንና የተገኙ ውጤ ቶችን፣ የቢሮ ዕቃዎችን አጠቃቀም ስታንዳርዳይዝ ለማድረግ የተከናወኑ ተግባራት፣ 35 ሺህ ሙት ፋይሎችን በመለየት፣ በማዛወርና በማከማቸት የተጀመረውን ሥራና ያጋጠሙ ችግሮችን በተመለከተ ውይይት ተደርጓል።

ከ1996 እስከ 1998 ዓ.ም ድረስ ለሦስት ዓመታት ሲሰራበት በነበረው ስትራቴጂክ ዕቅድ ተይዘው ከነበሩት ዓላማዎች መካከል በአደጋ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችል የዝግጁነት አቅም ይበልጥ ማጠናከር አንዱ እንደነበርና የዚሁ ዓላማ አንድ አካል የሆነው የወርሃዊ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መረጃ መሰብሰቢያ የማዘጋጀት ሥራ ከታቀደው መቶ በመቶ መከናወኑ፣ የመረጃ ጥራት ስለሚገኝበት ደረጃ የመስክ ግምገማ ለማድረግና የግምገማውን ሪፖርት አዘጋጅቶ ምላሽ (feed back) ለመስጠት ታቅዶ፣ በዓመቱ ውስጥ የመጡት መረጃዎች ተገምግመው ሦስት ምላሾች በሪፖርት መልክ ተዘጋጅተው ለክልሎች መሰጠቱ ተገልጿል።

ከዚህም በተጨማሪ በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ጥናት መሠረት መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማስተባበር የዕርዳታ ሀብት ግኝትን በማሳደግ የአደጋ ሰለባዎች ከቤት ንብረታቸው ሳይፈናቀሉ ሥርዓተ ያታን መሠረት ባደረገ መልኩ ምግብና ሌሎች መሠረታዊ ፍላጎቶችን በወቅቱ እንዲያገኙ በማድረግ እንዲሁም በጥናት ላይ ተመስርቶ ዕርዳታን ከልማት ጋር በማቀናጀት የአደጋ ተጋላጭነትን በመቀነስ አደጋን ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት በማገዝ ረገድ ባለፉት ሦስት ዓመታት ውጤታማ ሥራዎች መከናወናቸው ተገልጿል። የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራሞችን ተግባራዊ በማድረግ በኤጀንሲው ውስጥ ቀልጣፋ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓትንና ሥነ ምግባርን ማስፈን ያለፈው በስትራቴጂክ ዕቅድ አላማዎች እንደነበሩና በዚህም አበረታች ውጤት መመዝገቡ በሰነዱ ላይ ተመልክቷል። የዕርዳታ ንብረቶችን ደህንነት ጠብቆ መያዝና ዕርዳታውን ከወደብና ከማዕከላዊ መጋዘን ወደሚፈለግበት በማጓጓዝ ለተጠቃሚዎች ማድረስ፣ የሥርዓተ ያታ ግንዛቤ ማስጨበጪያ ትምህርት በመስጠትና፣ የአደጋ ተጋላጭነት ጥናት ሥራዎች መሰል ተግባራት ሲከናወኑ እንደቆዩና በድምር ውጤታቸውም ባለፉት ሦስት ዓመታት የተከሰቱ አደጋዎችን ለመቋቋምና የአደጋው ሰለባዎችን ለመታደግ መቻሉንም የ1996-1998 የስትራተጂክ ዕቅድ አፈፃፀምን የገመገመው ሰነድ አብራርቷል።

በአመዝኤ ዋና ዳይሬክተር ሲሞን መቻለ ሰብሳቢነት በተካሄደው በዚሁ ውይይት ላይ የመምሪያ፣ የቡድን፣ የዋና ክፍል ኃላፊዎችና ሌሎች የሚመለከታቸው የኤጀንሲው ሠራተኞች የተሳተፉ ሲሆን ለሰነዱ መዳበር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ሃሳቦችን በማቅረብና የታዩ ጉድለቶችን ከነማሻሻያቸው በመጠቆም ለአንድ ቀን የቆየ ሰፊና ጥልቅ ውይይት አድርገዋል።

በስትራቴጂክ ዕቅዱ ውይይት ላይ እንደተገለፀው የዕቅድ ዝግጅቱ ከሦስት ወራት በፊት አብይና የቴክኒክ ኮሚቴዎችን በማቋቋም የተጀመረ ሲሆን የስምንት የሥራ ዘርፎች ኃላፊዎች ተሳትፈውበታል።

## የበልግ ሰብል አዝመራና የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ሁኔታ ለመገምገም አጥኚ ቡድኖች ተሠማርተዋል

በበልግ አምራች አካባቢዎች ያለውን የሰብል አዝመራ ሁኔታ ፣ በአርብቶ አደር አካባቢዎች ደግሞ ከወቅቱ የዝናብ ሁኔታ ጋር በተያያዘ የሚታየውን የውኃና የግጦሽ ፣ የሰዎችና የእንስሳት ጤናና እንዲሁም ተዛማጅነት ያላቸውን የምግብ ዋስትና ሁኔታ የሚያጠኑ 17 ቡድኖች ከሰኔ 17 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ወደተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ተሠማርተዋል::

በአመዝኤ አስተባባሪነት የተሰማሩት አሥራ ሰባት አጥኚ ቡድኖቹ ለሦስት ሳምንታት ያህል በአማራ ፣ በትግራይ ፣ በኦሮሚያ ፣ በሶማሌና በአፋር ክልሎች የተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች በሚያደርጉት ቆይታ የበልጉ ወቅት በምግብ ዋስትና ረገድ ያስከተለውን አዎንታዊ ገፅታና አሉታዊ ተፅዕኖ የሚገመግሙ ሲሆን የተከሰቱ አደጋዎች ካሉ የፈጠሩትን ተፅዕኖ በማጥናት ሊወሰድ ስለማገባው እርምጃ የመፍትሔ ሃሳብ ያቀርባሉ:: በአርብቶ አደሩ አካባቢም የወቅቱ የዝናብ ሁኔታ ፣ በውኃና በግጦሽ ፣ በሰዎችና በእንስሳት ጤናና በገበያ አዝማሚያ ያሳየውን በጎ ለውጥና ተፅዕኖ በመመርመር አስቀድሞ ሊወሰድ ስለሚገባው እርምጃ በጥናታቸው አክለው እንደሚያቀርቡ ይጠበቃል::

በፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጅነት ኤጀንሲ /አመዝኤ/ አስተባባሪነት በሚካሄደው በዚሁ ጥናት ላይ ከአመዝኤ ፣ ከፌዴራል ምግብ ዋስትና ቢሮ ፣ ከውሀ ሀብት ልማት ሚኒስቴር ፣ ከግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ፣ ከዓለም ምግብ ኘሮግራም ፣ ከዓለም የምግብና የእርሻ ድርጅት (FAO)፣ ከሰብዓዊ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት (OCHA) ፣ ከአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (USAID) እንዲሁም ከሌሎች ለጋሽ አካላትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተውጣጡ 64 ባለሙያዎች ተሳታፊ ሆነዋል::

ባለሙያዎቹ ለጥናቱ ከመሰማራታቸው በፊት ሰኔ 16 ቀን 1998 ዓ.ም በመስክ ቆይ ታቸው ወቅት ጥናታቸውን ሲያካሂዱ ሊጠቀሙባቸው ስለሚገባ ስልቶች በምግብ ዋስትና ፅንስ ሀሳብና በአስቸኳይ የዕርዳታ ሥራ አይነቶች ላይ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ የግማሽ ቀን መግለጫና ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል::

በበልግ አምራች አካባቢዎች ያለውን የሰብል አዝመራ ሁኔታ ፣ በአርብቶ አደር አካባቢዎች ደግሞ ከወቅቱ የዝናብ ሁኔታ ጋር በተያያዘ የሚታየውን የውኃና የግጦሽ ፣ የሰዎችና የእንስሳት ጤናና እንዲሁም ተዛማጅነት ያላቸውን የምግብ ዋስትና ሁኔታ የሚያጠኑ 17 ቡድኖች ከሰኔ 17 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ወደተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ተሠማርተዋል::

## ባለፉት ሦስት ወራት ከ1.1 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተጓጉዟል

### ለሰኔ ወር ከ507 ሺህ ኩንታል በላይ ተመድቧል

ከመጋቢት እስከ ግንቦት 1998 ዓ.ም ባሉት ሦስት ወራት ውስጥ በተለያዩ ክልሎች ለሚገኙ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ፈላጊ ወገኖች እና ለሴፍቲኔት ኘሮግራም ተጠቃሚዎች በድምሩ 1 ሚሊዮን 180 ሺህ 616 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ተጓጉዞ በአብዛኛው ተከፋፍሏል::

ከዚሁ ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ ከተጓጓዘው ጠቅላላ የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 577 ሺህ 879 ኩንታል ለአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ፈላጊዎች የተጓጓዘ ሲሆን ቀሪው 602 ሺህ 737 ኩንታል ደግሞ በምግብ ዋስትና ቢሮ አማካይነት በተለያዩ ክልሎች ለሚገኙ የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች ተመድቦ በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ አማካይነት በአፋር ፣ አማራ ፣ ኦሮሚያ ፣ ደቡብ እና ትግራይ ክልሎች በሚገኙ 265 በላይ የሚሆኑ የማራገፊያ ጣቢያዎች የተጓጓዘ መሆኑን ከኤጀንሲው የንብረት አስተዳደርና ትራንስፖርት ማስተባበሪያ መምሪያ ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል::

ከመምሪያው የተገኘው መረጃ እንዳመለከተው በተለያዩ ክልሎች ለሚገኙ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ፈላጊዎችም የሚመደበው የምግብ

ዕርዳታ በየክልሉ እንደሚገኘው ችግር እና የተረጂ ህዝብ ብዛትን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሲሆን ፣ ለሴፍቲኔት ኘሮግራም የተጓጓዘውም ከድህነት ተላቀው ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ በየአካባቢያቸው በሁለቱም ዘርፎች ለተለያዩ ክልሎች የተጓጓዘው የምግብ ዕርዳታ በአብዛኛው ለተጠቃሚዎች መድረሱን መከፋፈሉንና ቀሪውም በመጓጓዝ ላይ መሆኑን ከመምሪያ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ ለአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ፈላጊዎች ከተጓጓዘው 577 ሺህ 879 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ ለሱማሌ 270 ሺህ 132 ፣ ለኦሮሚያ 212 ሺህ 649፣ ለአማራ 51 ሺህ 087 ፣ ለአፋር 15 ሺህ 972 ፣ ለጋምቤላ 7 ሺህ 530 እና ለድ ደዋ 4 ሺህ 829 ኩንታል ተጓጉዟል።



በአፈርና ውኃ ጥበቃ፣ በውኃ ማቆር፣ በእርከን ሥራና በመሳሰሉት የልማት ተግባራት በመሰማራት በሴፍቲኔት ኘሮግራም ከታቀፉ አርሶ አደሮችና ቤተሰቦቻቸው ቁጥር አኳያ መሆኑ ታውቋል። በዚሁ መሠረት ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ ለአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ፈላጊዎች ከተጓጓዘው 577 ሺህ 879 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ ለሱማሌ 270 ሺህ 132 ፣ ለኦሮሚያ 212 ሺህ 649፣ ለአማራ 51 ሺህ 087 ፣ ለአፋር 15 ሺህ 972 ፣ ለጋምቤላ 7 ሺህ 530 እና ለድ ደዋ 4 ሺህ 829 ኩንታል ተጓጉዟል። በተመሳሳይም በተለያዩ ክልሎች ለሚገኙ ሥር ከሰደደ ድህነት እንዲላቀቁና በዘላቂነት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከተነደፈው መርሀ ግብር አንዱ በሆነው፣ የሴፍቲኔት ኘሮግራም ተጠቃሚዎች ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ ከተጓጓዘው 602 ሺህ 737 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ ለአፋር 170 ሺህ 019 ፣ ለኦሮሚያ 165 ሺህ 730 ፣ ለአማራ 150 ሺህ 642 ፣ ለደቡብ ህዝቦች 61 ሺህ 827 እና ለትግራይ 54 ሺህ 517 ኩንታል የተጓጓዘ መሆኑ ታውቋል።

ይኸ በዚህ እንዳለ በተለያዩ ክልሎች የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ፈላጊ ለሆኑ ወገኖች ለሰኔ ወር በጠቅላላው 507 ሺህ 943.4 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል። ከዚሁ ለወሩ ከተመደበው የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 425 ሺህ 894.1 ኩንታል በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ቀሪው 82 ሺህ 049.3 ኩንታል ደግሞ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተመደበ መሆኑን ከኤጀንሲው የዕርዳታ ኘሮግራሞች አፈጻጸም ክትትል መምሪያ ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል።

ለየክልሎች የሚደረገው የዕርዳታ አመዳደብም በየክልሉ እንደሚገኘው ችግር ስፋትና ጥልቀት የሚለያይ ሲሆን በዚህ መሠረት ለሰኔ ወር ከተመደበው የምግብ ዕርዳታ ውስጥ ለሱማሌ 290 ሺህ 961.5 ኩንታል ፣ ለኦሮሚያ 161 ሺህ 631.7 ኩንታል ፣ ለአማራ 27 ሽህ 283 ኩንታል ፣ ለደቡብ ህዝቦች 9 ሺህ 498.9 ኩንታል ፣ ለአፋር 9 ሺህ 290 ኩንታል ፣ ለጋምቤላ 8 ሺህ 563 ኩንታል እና ለቤንሻንጉል ጉሙዝ 711.3 ኩንታል ተመድቧል።

# ከድርቅ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ የጤና ችግሮችን ለመከላከል የተደረገው የተቀናጀ ጥረት ውጤታማ እንደነበር ተገለፀ

በፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ አስተባባሪነት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና በተለያዩ ለጋሽ አካላት እንዲሁም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ድጋፍ በሶማሌ ክልል ከድርቅ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ የጤና ችግሮችን ለመከላከልና ለማከም የተደረገው የተቀናጀ ጥረት ውጤታማ እንደነበር የክልሉ ጤና ቢሮ ገለፀ።

ከድርቁ ጋር ተያይዘው የተከሰቱ የጤና ችግሮችን ለመከላከል የክልሉ ጤና ቢሮ ሥራውን የሚያስተባብር የአስቸኳይ ጊዜ ግብረ ኃይል ከማቋቋሙም በላይ በድርቁ በከፍተኛ ሁኔታ ከተጎዱት 24 ወረዳዎች ውስጥ ወደ 16ቱ ተንቀሳቃሽ የጤና ቡድኖችን በማሰማራት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ባደረገው የ52 የጤና ባለሙያዎች የህክምና መሣሪያዎችና መድሃኒቶች ድጋፍ ከድርቅ ጋር የተያያዙ የጤና ችግሮችን ለመከላከል መቻሉን ዶክተር አብዱልአዚዝ ኢብራሂም ገልፀዋል።



የክልሉ ጤና ቢሮ ምክትል ኃላፊ ዶክተር አብዱልአዚዝ ኢብራሂም ለአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የሕዝብ ግንኙነት ቡድን እንደገለፁት ዘንድሮ ተከስቶ የነበረው የዝናብ እጥረት ካስከተለው ድርቅ ጋር በተያያዘ የተከሰተው የምግብ እጥረት፣ ወባ፣ ኩፍኝና ሌሎች ውሃ ወለድ በሽታዎች በሕብረተሰቡ ላይ የከፋ ጉዳት ከማስከተላቸው በፊት በፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ አስተባባሪነት በዋናነት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ዩኒሴፍ ባደረጉት የባለሙያ የገንዘብና የህክምና የቁሳቁስ ድጋፍ መቆጣጠር ተችሏል።

በክልሉ ድርቁ በጀመረበት ጊዜ በጤና ተቋማት በቂ የህክምና ባለሙያዎችም ሆነ አስፈላጊው መድሃኒትና መሣሪያዎች እንዳልነበሩና ድርቁ ባስከተለው የሰውነት የመከላከል አቅም ማጣት ጋር የተያያዙ በሽታዎችና ኩፍቃ በተለይም በጋሻሞ፣ በደገሀቡርና በሀርሺን ወረዳዎች ተከስተው እንደነበር ያስታወሱት አብዱልአዚዝ መንግሥትና ተባባሪዎቹ ባደረጉት የተቀናጀ ጥረት አፋጣኝ ምላሽ በመገኘቱ ውጤታማ የሰዎችን ጤና የመከባከብና የመከላከል ሥራ በመሰራቱ አሳሳቢው ችግር ሊቀረፍ መቻሉን ተናግረዋል።

ከድርቁ ጋር ተያይዘው የተከሰቱ የጤና ችግሮችን ለመከላከል የክልሉ ጤና ቢሮ ሥራውን የሚያስተባብር የአስቸኳይ ጊዜ ግብረ ኃይል ከማቋቋሙም በላይ በድርቁ በከፍተኛ ሁኔታ ከተጎዱት 24 ወረዳዎች ውስጥ ወደ 16ቱ ተንቀሳቃሽ የጤና ቡድኖችን በማሰማራት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ባደረገው የ52 የጤና ባለሙያዎች የህክምና መሣሪያዎችና መድሃኒቶች ድጋፍ ከድርቅ ጋር የተያያዙ የጤና ችግሮችን ለመከላከል መቻሉን ዶክተር አብዱልአዚዝ ኢብራሂም ገልፀዋል።

አያይዘውም እያንዳንዱ እሽግ 5,000 ተጎጂዎችን ለ3 ወራት ለማከም የሚያስችል 64 የአስቸኳይ ጊዜ የሕክምና መሳሪያዎችና መድሃኒት **(Emergency Health Kits)** አቅርቦት በየወሩ ለጤና ተቋማቱ መከፋፈሉንና፣ በተጨማሪም እያንዳንዱ እሽግ 10 ሺህ ሰዎችን ለ3 ወራት ለማከም የሚያስችል 31 የአስቸኳይ ህክምናና የመድሃኒት ቁሳቁሶች ከፌዴራል ጤና ጥበቃ በመላኩ በሰዎች ላይ የተከሰቱ የጤና

ችግሮችን ለመከላከል ማስቻሉን አስረድተዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ለአራት ወረዳዎች 19 ሺህ 500 የወባ መከላከያ አጎበር ተከፋፍሏል። በ20 ወረዳ ለሚገኙ ህፃናት የቫይታሚን ኤ እደላና ከጥገኛ ትላትሎች ነፃ ማድረጊያ (deworming) መሰጠቱ እንዲሁም በእናቶችና በህፃናት ላይ የምግብ እጥረቱ የሚገቃበትን ደረጃ በማጥናት **(Nutritional Screening)** በተገኘው ውጤት መሠረት የልዩ ህክምና የምግባ ጣቢያዎችን **(Therapeutic Feeding Centers)** በመክፈት በተወሰደው እርምጃ እናቶችንና ህፃናትን ለመንከባከብ መቻሉን አብራርተዋል።